# የክቡር ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ

## 100ኛ ዓመት ልደት

## ሲመፖዚየም SYMPOSIUM

Saturday, October 17, 2009

Howard University, School of Engineering

Washington DC

**ከክቡር አቶ ሀዲስ አለማየሁ ጋር**

**በመማከረት ጉባዔ አባልነት ዘመናችን**

## ውድ የሲምፖዚየሙ ተሳታፊዎች !

ከሁሉ አስቀድሜ ኢትዮጵያ ሀገራችን በሃያኛው ምዕተ ዓመት ከአፈራቻቸው ታላላቅ ሰዎች መካከል አንፀባራቂ ኮከብ የነበሩትን የክቡር አቶ ሀዲስ አለማየሁን የአንድ መቶ ዓመት የልደት በዓል ለማክበር ይህን ሲምፖዚየም ላዘጋጀው ኮሚቴ ምስጋናየን አቀርባለሁ ። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጀግና እየተረሳ ፥አርበኛ እየከሰመ ፥ ሀገር ወዳድ እየደከመ ፥ ደራሲ እየመነመነ ፥ የሕዝብ ተቆርቋሪ እየተሸማቀቀ ባለበት ወቅት፥ ስማዕታት ኢትዮጵያውያንን መዘከር የዛሬውት ውልድ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ፥ የዜግነት ግዴታውም እንደሆነ ይታመናል ። እኔም ስለእኝህ ታላቅ ሰው በመጠኑ የማውቀውን ለመመስከር ዕድል በማግኘቴ የተለየ ክብርና ደስታ ይሰማኛል።

ከክቡርነታቸው ጋር ለመገናኘትና ለመተዋወቅ ፥ ብሎም የቅርብ ወዳጅነት ለመመስረት የቻልኩት በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ነበር፡ ፡ ይህም በየካቲቱ 66 ዓ.ም. ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ወቅት ነው ። ከዳር እስከዳር ለውጡን የተቀበለው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ሀገራችን በሰላማዊና በተረጋጋ ሁኔታ ለውጡን ተቀብላ መራመድ አለበት የሚል ዕምነት ነበረው።በመሆኑም፥ከአሮጌው ሥርዓት ወደ አዲስ ሥርዓት ለመሸጋገር ባህሏን ታሪኳንና ዕምነቷን ጠብቃ መጓዝ አለባት ተብሎ ተስፋ ተደረገ ። ተስፋን ዕውን ለማድረግ ካስፈለገ ፥ለአዲሱ ሁኔታ የሚስማማ ሕገ መንግሥት መዘጋጀት ይኖርበታል የሚል የሕዝብ ጉጉት ተከሰተ ። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሀገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት ሊያረቅቅ የሚችል ሕገመንግሥት አርቃቂ ጉባዔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ተመረጠ ። የሸንጎው ተቀዳሚ ተልዕኮና ዓላማ ፥ ኢትዮጵያ ከፊውዳል ሥርዓት ወደ ዴሞክራቲክ ሥርዓት ልትሸጋገር የሚያስችላትን ሕገ መንግሥት መቅረፅ ነበር ። ጉባዔውም የመማክርት ሸንጎ የሚል ስያሜ ተሰጠው ። በዚህ መሠረት የአስራ አራቱ ክፍለተ ሀገር ሕዝብ ወኪሉን መረጠ ወደ አዲስ አበባ ላከ ። እንዲሁም ፥ ከልዩ ልዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች የተወከሉ ፥ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን ፥ ከኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር ፥ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተክርስቲያን ፥ከኢትዮጵያ እስላሞች፥ ከኢትዮጵያ ነጋዴዎች መምክር ቤት ፥ ከጭላሎ የርሻ ድርጅትና ከወላይታ የርሻ ድርጅት የተመረጡ ተወካዮችን የያዘ ጉባዔ ተመሠረተ። ክብር አቶ ሀዲስ አለማየሁም በጎጃም ሕዝብ ተመርጠው ወደ መማክርት ጉባዔው መጡ ። በምክር ቤቱ ውስጥ የአባላቱ የአቀማመጥ ሥነሥርዓት የተመደበው፥ በመጀመሪያ ስማቸው የአማርኛ ፊደል ተራ ስለነበር ፥እኔም ከእርሳቸው ኋላ ባለው የመስመር ተራ እንደቀመጥ ዕድል ገጠመኝ ። የመማክርቱ ጉባዔ አባላት ሥራችንን ለመቀጠል እንዲያስችል በአምስት የተግባር ኮሚቴዎች ተመደብን ። አሁንም ክቡር አቶ ሀዲስና እኔ በፖሊቲካና ሕግ ኮሚቴ ስር ተመደብን ሥራችንን ቀጠልን ።እንግዲህ በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ነበር እኝህን ታላቅ ኢትዮጵያዊ ለመተዋወቅና ማንነታቸውን ብቅርብ ሁኜ ለመረዳት መልካም ዕድል ያገኘሁት ።

በዚህ ሁኔታ ከክቡር ሀዲስ ዓለማየሁ ጋር ለሁለት ዓመት በመማክርቱ ጉባዔ ውስጥ አብረን ቆይተናል ። ጊዜው ከ1967 መጀመሪያ እስከ 1968 ዓ.ም.መጨረሻ ነው ። ታዲያ ዛሬ በዚህ ሲምፖዚየም ቆሜ ስለክቡርነታቸው የምመሰክረው ቃል፥ከእርሳቸው

የሰማሁትንና እኔም ጠይቄ ከራሳቸው ልሳን ያዳመጥኩትንና የተረዳሁትን፥ እንዲሁም ከሁለታችን የግል ጭውውት የማስታውሰውን ይሆናል ። አጽንዖት ለመስጠት የምሞከረውም ፥ የክቡረነታቸው ሰብዕናም ሆነ ተግባር ፥ በኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ ትቶት ባለፋቸው አንዳንድ ትዝታዎች ብቻ ላይ ይሆናል።በመሆኑም የክቡርነታቸውን ሙሉ የሕይወት ታሪክ ለመናገር ብቃቱ ይኖረኛል ብየ አልቃጣም ።ይህንን ሊፈጽሙ የሚችሉ ሌሎች ሰዎች አሉ ብየ ግን አምናለሁ ። የሀገራችንን ታሪክ ፥ እንዲሁም ፖለቲካዊ፥ ማኅበራዊና ባኅላዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ ከአቶ ሀዲስ የቀሰምኩትን ትምሕርት ከሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አላገኘሁም ። ወደፊትም አገኘሁ ይሆናል ብየ ለማሰብ የሚቸግረኝ ይመስለኛል ። ከክቡር አቶ ሀዲስ አለማየሁ ጋር የተወሰነ ጊዜ በማሳለፌ ፥ በዕርግጥም ዕድለኛ ነበርኩ ።

ክቡር አቶ ሀዲስ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚወዱ ፍቅራቸውንም በትውር ብቻ ሳይሆን ፥ በሚያኮራ ተግባርና መሥዋዕት ያስመሰከሩ ታላቅ ሰው ነበሩ ። በግል ሕይወታቸውም ከፍተኛ የሞራል ልዕልና በተጎናጸፈ አርዓያ የገለፁ ሰው ናቸው። ሰብዕናቸውም ራስን በመውደድ ፥ በወዳሴ ከንቱና በቀቢፀ-ተስፋ የተመሰረተ አልነበረም ። ወደ ስድሳ ዓመታት ያህል ሀገራቸውን በአገለገሉበት የሥራ ዘርፍም ግዙፍ የሆነ ወጤትን ያስመዘገቡና ታላቅ ብሔራዊ ተግባር የፈፀሙ ሰው ነበሩ።

የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከሀገራችን ከተባረረ በኋላ፥ ዐፄኃይለ ሥላሴ አዲስ መንግሥት ሲያዋቅሩ ፥ክቡር አቶ ሀዲስ ዓለማየሁ፥ ለሀገራቸን፥ በቅድሚያ ከሚታሰቡት ውስጥ መሠረታዊ ሆነው ካገኟቸው አጣዳፊ ጉዳዮች መካከል፥የኢትዮጵያን የውጭ ፖሊሲ መቅረጽና በተግባር መተርጎም አንዱ እንደነበረ በኮሚታችን ውስጥ ሲያስረዱ አዳምጫለሁ ። ይህ ዕምነታቸው በቅርብ በሚያውቋቸው የውጭ ሀገር ሰዎች ዘንድ ፥ ሳይቀር የዘመናዊቷ ኢትዮጵያን የወጭ ፖሊሲ ከቀረፁት ሰዎችመካከል አንዱ ነበሩ ተብለው እንደተመሰከረላቸው፥በአስረጅነት እኮሚቲያችን ተጋብዘው ከመጡት ሰዎች ልሳን ሰምቻሉ ። እንደ ክቡርነታቸው ዕምነትና በኋላም በተግባር ተተርጉሞ እንደ ታየው ፥ የሀገሪቱ ዲፕሎማሲ መመስረት ያለበት ፥ በአወንታዊ ገለልተኛነት ላይ ማለት ( በፖዜቲቭ ኒውትራሊቲ ) ነው ብለው የሚያምኑ ነበሩ ። በክቡርነታቸው ራዕይ፥ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ መቃኘት ያለበት፥ የሀገሪቱን ሉአላዊነት፥ የግዛት አንድነትና የፖሊቲካ ነፃነት በሚያስከብርና የዜጎቿንም ዘላቂ ጥቅሞች በሚያስጠብቅ አቋም ሆኖ ፥ባህሏን ዕምነቷን ፥ ክብሯን ፥ታሪኳንና ጥንታዊነቷን የሚያስከብርላት እንጅ ፥ ከማነኛውም ርዕዮተ-ዓለምም ሆነ ከየትኛውም ካምፕ ወይም ኃይል ጋር መወገን የለበትም ባይ ነበሩ ። ዛሬም፥ በለውጥ ሂደት ውስጥ የምትገኘው ሀገራችን ፥በአወንታዊ ገለልተኝነት ላይ የተመሰረተ ነፃ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ማካሄድ አለበት ብለው በኮሚቲያችን ውስጥ አሳብ ሲያቀርቡ ሰምቻሉ። ይህ ፖሊሲ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ፥በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ፖሊሲ ብትከተል ፥የዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲዋ የተከበረና የታፈረ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ፖሊሲዋም ለአለፉት አምሳ ዓመታት በተግባር ተተርጉሞ ከፍተኛ ውጤትን አስመዝግቧል ብለውናል ።ለማነኛውም የውጭ ኃይል ያላጎበደደና ለየትኛውም ሀገር ተጽዕኖ ያልተልፈሰፈሰ ነፃና ገለልተኛ የውጭ ፖሊሲን በተግባር መተርጎም፥ የኢትዮጵያ ሀገራችን ዓይነተኛ መመሪያዋ መሆን አለበት ብለው የሚያምኑ ባለ ታላቅ ራዕይ ሰው ነበሩ ። የኢትዮጵያ ዐብዮትም ኢትዮጵያዊ ሆኖ ከቀጠለ ያመረቃ

ውጤት ሊያስመዘግብ ይችላል ብለው ከልብ ያምኑ ነበር ። ከዚህም መሠረታዊ ዕምነት በመነሳት፤ ሀገራችን ፥ የገለልተኛ ሀገራት ጉባዔን ከመሰረቱት ስድስት ሀገሮች አንዷ እንደ ነበረች ለኮሚቲያችን ሲያስረዱ አዳምጫሉ ። ኢትዮጵያ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ስትመራበት የነበረው የውጭ ፖሊሲ የሀገራችንን ዲፕሎማሲና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ፥ በከፍተኛ ደረጃ ያስከበረላት ፥ ተአማኒነት ያተረፈላትና ብሎም በተለያዩ የዓለም አቀፍ መድረኮች ግንባር-ቀደም ሚና እንድትጫዎት አድርጓታል ብለውናል ፥ ክቡር አቶ ሀዲስ !

የውጭ ፖሊሲ ባለሙያዎችና የዲፕሎማሲ ጠበብት እንደሚሉት ፥ የአንድ ሀገር የውጭ ፖሊሲ ፥ የዚያው ሀገር የውስጥ ፖሊቲካ ቀጥተኛ ነፀብራቅ ነው ይባላል ። የአንድ ሀገር የውስጥ ፖሊቲካ ፥ የውጭ ፖሊሲው ነፀብራቅ መሆኑን በሚገባ የተገነዘቡት ክቡር አቶ ሀዲስ አለማየሁ ፥ የሀገሪቱ የውጭ ፖሊሲ የተሳካ ውጤት ሊያስመዘግብ የሚችለው ፥ የውስጥ ፖሊቲካዋ በግድ መሻሻልና አስተዳደሩም ዲሞክራሲያዊ ሲሆን ብቻ ነው ብለው ከልብ ያምኑ እንደ ነበር ዘርዝረው አስረድተዋል ። ይህም ዕውን እንዲሆን የተቻላቸውን ያህል ሲጥሩ የኖሩት በዚህ መሠረታዊ ዕምነታቸው እንደ ነበር ተናግረዋል። ለሀገሪቱ ታላቅ ራዕይ የነበረው ይህ ሕገመንግሥት አርቃቂ ጉባዔ የሚሰራውን ተግባር ግን የደርግ ሰዎች ፈጽሞ አልወደዱትም ። አኳኋኑም ስላላማራቸው ጠሉት። አባላቱንም ቀስ በቀስ ማጥፋት ጀመሩ።

ክቡር አቶ ሀዲስ ዓለማየሁ፥ ለሚወዷት ሀገራቸው ያበረከቱት አገለግሎት ፥ ፖሊሲ በማውጣት ላይ ብቻ ሳይወሰን ያወጡትንም ፖሊሲና መመሪያ በተግባር በመተርጎም ጭምር ግምባር ቀደም ሚና የተጫወቱ ነበሩ ። በተለያዩ የዓለም አቀፍ ጉባዔዎች የኢትዮጵያን መልዕክተኞች በመምራት የሀገራችንን ስትራተጃዊ ጥቅሞች የሚያስጠብቁ ውሳኔዎች እንዲተላለፉ አስደርገዋል ። የንጉሠ ነገሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደርና ልዩ መልዕክተኛ ሆነው በተመደቡባቸው ሀገሮች ፥ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥሪያ ቤት በኒውዮርክ ፥ በብርታንያ ፥ በእስራኤልና በሌሎቹም ከተሞች፥ሀገራቸውን የሚያኮራ ተግባራትን እንዳስመዘገቡና ይህ ክስተት ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ሊጠቅማት እንደሚችል ለማስረዳት ሞክረዋል ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ ሆነው በኒው ዮርክ ከተማ በቆዩባቸው በርካታ ዓመታት ፥ የሀገራቸውን ዘለቄ ጥቅም ለማስጠበቅ ከልባቸው እንደጣሩ በማስረጃ የተደገፈ ምስክርነት ሰጥተዋል።በመርኅ ላይ የተመሠረ ተጠንካራ አቋም በማሳየታቸው፥በወቅቱ የድርጅቱ ዋና ፀሃፊ የነበሩት ሰው ሲያውኳቸው እንደ ነበረና፥ እንዲያውም እኝህ ሰው አልፈው-ተርፈው በየጊዜው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ እየደወሉ ሲያሳጧቸው እንደ ነበር ክቡር ሀዲስ አጫውተውናል። ከዚህ ጋር በማያያዝ የአንድ ሀገር መሪ፥ምንም ቢሆን ፥ ከውጭ ሀገር ዜጋ ይልቅ የራሱን አምባሳደር ማመን ተገቢ መሆኑን አስረድተዋል ። የአቶ ሀዲስ ጠንካራ ሰብዕና ግን በመርኅ (በፕርንስፐል) ላይ ከተመሰረተው አቋማቸው ፍንክች ላለማለት በእጅጉ እንደረዳቸው ነግረውናል።

በዲፕሎማቲክ መስክ ከአበረከቱት ግዙፍ አገልግሎት ባሻገር ፥ ክቡር አቶ ሀዲስ፥ በተለያዩ ጊዚያት በሚኒስትር ማዕረግ ሀገራቸውን በትጋት፥ በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል። በተለይ ፥ የትምህርት ሚኒስቴርንም ሆነ የፕላኒግ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን በኃላፊነት በመሩባቸው ወቅቶች ዕንከን ያልወጣለት ችሎታቸውን በርዓያነት አስመስክረዋል ። ሠራተኛንና ሥራን አገናኝቶ ሰርቶ በማሰራት ከሚመሰገኑ ባለሥልጣኖች አንዱ እንደነበሩ ለአስረጅነት ወደ ኮሚቲያችን የመጡት ባለሙያዎች ሁሉ መስክረውላቸዋል ። እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ሊወገድ ባልቻለው ተውሳክ ፥ ማለት በወገን ፥በዘመድ፥በቤተስ፥በጋብቻ፥ በዘርና፥በአማላጅ ሳይሆን የክቡርነታቸው የአመራር መርህ የተመሠረተው በችሎታ ( Meritocracy)ላይ ብቻ ነበር። የታህሳሱ 53 ዓ.ም. የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ከከሸፈ በኋላ በተደረገው የሚኒስትሮች ሹም-ሽር ፥ ክቡር አቶ ሀዲስ የትምህርት ሚኒስቴርን እንዲመሩ ተመድበው ነበር ። ሥርዓተ-ትምህርቱንና የመማሪያ መፃህፍት ለማሻሻል የነበራቸው ዕቅድ ግን በአጭሩ ተቀጭቶባቸዋል ። ይህም የሆነው በለውጥ ፈላጊው ክፍል ዘንድ ፥ፋና- ወጊ መሆናቸውን የሚመስክርላቸውን ንግግር በማድረጋቸው ነበር ። ንግግራቸውን እጠቅሳለሁ፥

“ ሰው እንደ ቤቱ እንጅ፥ እንደጎረቤቱ አይኖርም የሚለው አባባል ፥ያረጀ-ያፈጀ አመለካከት ነው። ሰው እንደ ጎረቤቱ ለመኖርና ለመሻሻል መጣጣር ይኖርበታል ። ” በማለት በአደባባይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ያሰሙት ንግግር ፥ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቤተ መንግሥት ዘንድ ሳይወደድላቸው በመቅረቱ ፤ ወዲያውኑ ከሥልጣናቸው ተነስተው ፥ በአምባሳደርነት ወደ ውጭ ሀገር እንዲሄዱ ሆኗል ። የክቡርነታቸው ወደ ውጭ መላክ ግን ለሀገሪቱ ችግር መፍተሄ አልነበረም ። እንዲያውም የሀገሪቱ ችግር እየተባባሰ ነበር የሄደው።

ክቡር አቶ ሀዲስ ዓለማሁ ለሀገራቸው የነበረቻው ራዕይ ፥ ከአድማስ ባሻገር ስለነበረ፥ ለዲሞክራሲ፥ለፍትኅ-ርትዕ፥ ለብልፅግና፥ ለዕድገትና ለሥልጣኔ አጥብቀው የሚመኙ ብቻ ሳይሆን ፥ በሥራ ተተርጉሞ ለማየት አቅማቸው የሚፈቅድላቸውን ሁሉ አድርገዋል ። ለሀገር ይጠቅማል የሚሉትን ሁሉ ከትውር እስከ ድርጊት ሞክረዋል ። ለሀገር ይበጃል ብለው ያመኑትን ሁሉ ሳይፈሩና ሳይቸሩ ፥ ሊያስከትልባቸው የሚችለውንም ማንኛውንም አደጋ በግምት ውስጥ ሳያስገቡ ለንጉሠ ነገሥቱም ሆነ ከእርሳቸው በኋላ ለተተካው የደርግ ሥርዓት በድፍረት ከማቅረብ አልተቆጠቡም። ሥርዓቶቹ ስለአለፈቀዱላቸው ግን ራዕያቸው ዕውን ሊሆን አልቻለም።

ይህንንም በሚመለከት:-

1ኛ) እርሳቸው በግል የነገሩኝንና ያሳዩኝንም ሰነድ

2ኛ) እኔ በዓይኔ ያየሁትን አጠር አድርጊ ለመናገር እሞክራለሁ።

1. የታህሳሱ 1953 የመንግሥት ግለበጣ ከከሸፈ በኋላ ክቡር አቶ ሀዲስ ለንጉሡ በድፍረት ያቀረቡትን የአስተዳደር ማሻሻያ ባለ 13 ገጽ ሰነድ በመኖሪያ ቤታቸው በሚገኘው ጽ/ ቤታቸው ውስጥ አስነብበውኛል። “ታዲያ የዚህ ሰነድ

ዕድል ምን ሆነ?" ብይ ብጠይቅኋቸው ። የሚከተለውን መልስ አግኝቻለሁ። አጠቅሳለሁ።

" ጃንሆይ ሰነዱን ካነበቡ በኋላ ጠቅላይ ምኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድን፥ ጄኔራል አቢይ አበበንና እኔን አነጋገሩን ። በሰነዱ ላይ ተመርኩዘን ለሀገርና ለመንግሥት የሚጠቅም የተግባር ዕቅድ እንድናቀርብ በማዘዝ ሰነዱን እፊታችን ላይ ለጠቅላይ ምኒስትሩ ሰጧቸው። ጄኔራል አበበም፥ ጃንሆይ፥ይህ ሥራ ከባድ ስለሚሆን ተጨማሪ ሰው ይታዘዘልን በለው ኃሳብ አቀረቡ ። ጃንሆይ ግን ፈቃደኛ አልሆኑም። ጄኔራል አበበም እንደገና ባይሆን በፀሐፊነት እንዲረዳን ከተማ ይፍሩ ይመደብለን ብለው አሳሰቡ ። ጃንሆይም በኃይል ቃል፥ የለም እናንተ ብቻ ትበቃላችሁ በለው አሰናበቱን ። ከዚያ በኋላ ሰነዱ የት እንደገባ ሳይታወቅ ቀረ ። " ብለው አቶ ሀዲስ መልሰውልኛል።

2. በደርግ ጽ/ ቤት የተደረገ ፍጥጫ

አንድ ቀን የደርግ ወታደሮች የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞችን ማኅበራቸው ያሳለፈውን ውሳኔ የያዘ ወረቀት ብትናችኋል በማለት በሌ አየር ማረፊያ አካባቢ ተኩስ ከፍተው ይገድሏቸዋል ። ብሄራዊ ሸንጎው ግድያውን በቃወም የውግዘት ውሳኔ የያዘ ደብዳቤ ለደርግ ይልካል ። የሸንጎው ውሳኔ ያስቆጣቸው ደርጎች፤ ዛቻን የተላበሰ ደብዳቤ በመንግሥቱ ኃይለማርያም ተፈርሞ ወደ ሸንጎው ይላካሉ። ሸንጎው በተላከው የደርግ ደብዳቤ ላይ ከተወያየ በኋላ ጥቂት አባላትን የያዘ ልዑክ ወደ ደርግ ጽ/ ቤት ሄዶ ስለ ጉዳዩ እንዲነጋገር ይወስናል። በውሳኔው መሠረትም ፥አቶ ሀዲስ ዓለማየሁ፥አቶ አሰፋ ሊበን ፥አቶ መንግሥቱ ለማ ፥አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ ፥አቶ በየነ አብዲና ተገኘ ሞገስ ወደ ደርግ ጽ / ቤት በመሄድ ከመንግሥቱ ኃ/ ማርያምና ሌሎች ሁለት የደርግ አባላት ማለትም ከሻለቃ ፍስሐ ደስታና ከመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ ጋር ይገናኛል ። ሦስቱም ሽጉጥ አገልደመው ወደ አዳረሹ ይገባሉ። ሁኔታው በፀጥታ ብቻ ሳይሆን፥በፅልመትም የተሸፈነ ነበር። የዚህን ፅልመት ጭጋግ የገፈፉት ክብሮ አቶ ሀዲስ ነበሩ ። ከተላክነው ሰዎች ውስጥ መጀመሪያ የተነገሩት እርሳቸው ሆኑ። ጥበብን ፥ማስተዋልን ፥ ድፍረትንና ለዘብታን በተላበሰ አነጋገር "ሻለቃ መንግሥቱ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ እኮ በሚገባ አታውቁትም ። በኃይል ለመግዛትም ያስቸግራችኋል። ሰው መግደሉ ይቆም። " ብለው ተናገሩ ። መንግሥቱም በበኩሉ፥ " ትላንት የፀጥታ ጠባቂ ወታደሮች የፈፀሙት ድርጊት ሁላችንንም አሳዝኖናል።" ካለ በኋላ "ቢሆንም እኮ ዐብዮት ልጇን ትባለለች ይባል የለ እንዴ? " ሲል በትዕቢት የተመላ ምፅት ተናገረ ። ስብሰባውም ያለ አንዳች እልባት አለቀ። ከሁለት ሰዓታት ፍጥጫ በኋላ እኛ ወደ ሸንጎው ተመልሰን ሄደን የሆነውን ሁሉ ለጠቅላላው የሸንጎ ስብሰባ አስረዳን።

ክቡር አቶ ሀዲስ ፥ ትክክለኛ ነው ብለው ያመኑበትንና ከኀሊና ወቀሳ ነፃ የሚያደርጋቸውን ዓላማና ተግባር፥ እንዲሁም ለሀገር ይጠቅማል የሚሉትን ኃሳብ ሁሉ ያለ አንዳች ስጋትና ያለ እበላ ባይነት ለሀገሪቱ መሪዎች ማቅረብ መተከላዊ

መርሆአቸው ስለነበር ፤ በዚያ በሚያስፈራው በደርግ ዘመን እንኳ ቢሆን ይህንን ከመፈፀም አልታገዱም::

ክቡር አቶ ሀዲስ ደርግ ይቀበሉ ያላቸውን የጠቅላይ ሚኒትርነቱን ቦታ ለምን እንዳልተቀበሉ ስንጠይቃቸው ፥እንደሚከተለው ነግረውናል::

" አንድ ቀን ጄኔራል አማን በስልክ ጠራኝና ተገናኘን :: ደርጎቹ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ እንዲይዙልን ጠይቅልን ብለውኛል ብሎ ነገረኝ :: እኔም አስቤ አስውቃለሁ ብየ መለስኩለት:: ለመልሱ እንድነገናኝ በቀጠሮ ተለያይን:: በቀጠሯችን ስንገናኝ ፥መላውን የኢትዮጵያ ህብረትሰብ የሚወክሉና የሠራዊቱንም ተጠሪዎች የያዘ ጊዚያዊ የመሽጋገሪያ መንግሥት ይቋቋምና በዚህ ሂደት ውስጥ ያቅሜን አስተዋፅዖ አድርጋለሁ :: ከዚያ በፊት ግን ወታደሩ ወደ ጦር ሰፈሩ መመለስ ይኖርበታል :: ብየ መለስኩለት:: በማግስቱ ደርግ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ሀዲስ አለማየሁ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ተጠይቀው ፈቃደኛ አልሆኑም የሚል ዜና ሰማሁ :: ጉዳዩ በዚህ አበቃ :: " ብለው ለኮሚቲያችን መልሰዋል::

የክቡር አቶ ሀዲስን ሰብዕና በትክክል የሚገልጹ ናቸው ብየ የተዘብኳቸውን አንዳንድ በግል ያጫወቱኝን አጋጣሚዎች ልናገር እፈልጋለሁ::

- ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ በኢጣሊያ ደሴት ተግዘው በነበሩበት ወቅት ከአጋጠሟቸው የተለያዩ ክስተቶች ውስጥ በርከት ያሉትን ቢነግሩኝም፥ እኔ ግን ዛሬ አንዱን ብቻ መርጨ ልናገር እፈልጋለሁ::

ይህም፥ ከፍተኛ የውሀ ዋና ችሎታቸውን የገለፁበት አጋጣሚ ነበር :: በሮማ ዩኒቨርቲ ስትማር የነበረች አንዲት ወጣት ኢጣሊያዊት በበጋ ወራት እናቷን ለመጠየቅና የዕረፍት ጊዜዋን ለማሳለፍ እነ አቶ ሀዲስ ተግዘውበት ወደነበረው ደሴት ትመጣለች :: ከግዞተኞቹ ኢትዮጵያውያን መካከል አንድ ዘመናዊ ትምህርት ከተማሩ ሰው ጋር ጓደኝነት ትመሰርታለች :: ጓደኝነታቸው እየጠነከረ - እየጋለ ይሄዳል :: ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያዊው ግዞተኛና ይህች ወጣት ጣሊያናዊት በበህሩ ዳርቻው ሁልጊዜ ይንሽራሽራሉ ::ይህን ተመለክቶ የቀና አንድ ኢጣሊያዊ ወጣት መኮንን፥ " ከዚህች ልጅ ጋር ሁለተኛ እንዳላይህ ፥ እኔ ፍፈልጊያታለሁና :: አሻፈረኝ ካልክ ፥ ሁለታችን ይዋጣልን :: ቡጢ እንግጠምና ያሸነፈ የርሷ ጓደኛ ይሆናል " ብሎ ለኢትዮጵያዊው ግዞተኛ የይዋጣልን ማስጠንቀቂያ ይሰጣል:: ይህንን ጉዳይ እኝህ ግዞተኛ ለጓደኛቸው ለክቡር አቶ ሀዲስ ያዋዩዋቸዋል :: ክብሩ አቶ ሀዲስም በበኩላቸው ለይዋጣልኑ ድንፋታ እንዳይበገሩ ጓደኛቸውን ያበረታታሉ:: ጎደኛቸውም "እኔ ይህን የኢጣሊያ መኮንን በቡጢ አልችለውም " ብለው ስጋታቸውን ይገልጹላቸዋል :: አቶ ሀዲስም፥ " በቡጢ ሳይሆን በውሃ ዋና እንጋጠም በለህ ጠይቀው::" ይሏቸዋል:: ጓደኛቸውም " ወሃ ዋናውንም እኮ አልችልበትም :: " ብለው ይመልሱላቸዋል :: ክቡር አቶ ሀዲስም " ግዴለም ፥ ብቻ ጣሊያኑ በውሀ ዋና ውድድር ይስማማ እንጅ እኔ ስለአንተ ሆኘ እግጥመውና አሸንፈዋለሁ:: " ይሏቸዋል :: ጓደኛቸውም ፥

" ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ?ጉዳዩ የኔ ነው:: እኔኑ እኮነው ጣሊያኑ ይዋጣልን ያለኝ:: " አሏቸው:: እንግዲህ ያቶ ሀዲስ አለማየሁ የተራቀቀ ዘዴ የሚታየው እዚህ ላይ ነው:: " አንተ ራስክን በኢትዮጵያ ውስጥ ሳለህ የሀገሪቱ የውሀ ዋና ሻምቢዮን እንደነበርክ ግለጽለና ጣሊያኑ ከአንተ ከኢትዮጵያው ሻምፒዮን ጋር ከመወዳደሩ በፊት ፥ ከሀዲስ ጋር ተወዳደርና ሀዲስን ካሸነፍክ ከኔ ጋር ተገጥማለህ ብለህ በለው " ይሏቸዋል:: ጣሊያኑ በዚህ ይስማማል :: የውድድሩ ቀን አንድ እሁድ ከሰዓት በኋላ እንዲሆን ይወሰናል :: ኢትዮጵያውያን ግዞተኞች፥ የልጅቷ ቤተሰቦችና የአካባቢው ነዋሪ ወደ ባህሩ ዳርቻ ውድድሩን እንዲመለከት ይጋበዛል:: የውድድሩ ርቀት በባህሩ ውስጥ በብቸኝነት የቆመችውን ቋጥኝ ነክቶ መመለስ እንዲሆን ይወሰናል:: የውድድሩ ዳኛ ፥" ኡኖ! ዱዌ! ትሬ ብሎ ከቆጠረ በኋላ የያዘውን የስፖርት ሽጉጥ ተኩሶ የዋናውን ውድድር እንዲጀምሩ፥ የኢጣሊያኑን መኮንንና አቶ ሀዲስን ይለቅቃቸዋል:: ክብሮ አቶ ሀዲስ በማይታመን ፍጥነት ቋጥኟን ነክተው በመመልስ ተወዳደሪያቸውን በማሸነፍ ፥ ለጓደኛቸው ሚች ብቻ ሳይሆኑ፥ የግዞተኞችንም ክብር አስረግጠዋል:: አባሾቹ ግዘተኞችም፥ " ብር አምበር ሰበረልሽ፥ ኢትዮጵያ ልጅሽ" እያሉ ወደ የክፍላቸው ገቡ:: ብለው ነግረውኛል::

ክቡበር አቶ ሀዲስ ፈጥኖ የማሰብና ወዲያውኑ ትክክለኛ ውሳኔና መልስ መስጠት የሚችል ፈጣንና ብሩኅ እዕምሮ የነበራቸው ሰው ነበሩ:: አንድ ቀን በፓርላማው ውስጥ በሚገኘው ካፌቴርያ ውስጥ ሁለታችን ቡና እየጠጠን እያለን፥ ተቀናጠሁ ብየና ፥አቅሜንም ሳላውቅ ምናልባትም፥ " የቄስ ሚስት አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጽሃፍ አጠበች:: " እንደሚባለው ተርት ሆኖብኝ ነው መስል ፥ በአንድ ነገር ተተናኮልኳቸው ፥ እንዲሁም አልኳቸው::

" ጌታዬ፥አንድ የጎጃም ጎረምሳ ፍቅረኛውን ምን እንዳላት ሰምተዋል?" አልኳቸው:: "ምን አላት?" አሉኝ::

"ጎጃሜ ቡዳ ነው ብለሽ አውርተሻል፥
ሰውን ሰው ሲበላው የት አባሽ አይተሻል?"
ብሎ አላት ብየ ስላቸው፥
ከመቅጽበት የሚከተለውን መልስ ሰጡኝ::

" እንዴ? ታዲያ፥ ቡዳ ነው ቢሉትም ጎጃሜውን ሁላ፥
ፍቅር የት ይገኛል ሰው አንጀት ከአልበላ፥ ብሎ አይጨምርበትም ነበር ? "
ብለው ፈጣን መልስ ሰጡኝ :: እኔም አፌን በዳቦ ብየ ቀረሁ ::

የክቡር አቶ ሀዲስን ሰብዕና የተለየ ክብርና ሞገስ ከሚያስለግሳቸው መካከል አንዱ ፥ስለ ጋብቻ ቅዱስነት፥ ስለ ዕውነተኛ ፍቅርና ፥ ስለ ትዳር ክብር የነበራቸው ፅኑ ዕምነትና ያሳለፉት እንከን የሌለው ህይወት ነበር ። በግል እንዳጫወቱኝ ፥ ክቡርነታቸው ለፍቅር ያላቸው ዕምነት ፥ማለትም፥ "ፍቅርን" የሚያዩት "እስከ መቃብር" ድረስ ብቻ ሳይሆን ፥ ከመቀብርም ባሻገር ተራምዶ በማለፍ፥ የሙታንን ዓለም ዘልቆ በሄደ ትዝታም ጭምር ይመስለኛል ። ለክቡርነታቸው ጋብቻና ፍቅር ለህይወወታቸው አልፋና ኦሜጋ እንደ ነበረ በህይወታቸው ዘመን ሁሉ አስመስክረዋል ። ለክቡርነታቸው ፥ የመጀመሪያም የመጨረሻም ለሆነው ጋብቻቸው የተለየ ክብርና ፍቅር ስለነበራቸው ክብርት ባለቤታቸው ወይዘሮ ክበበ ፀሐይ ከሞቱባቸው በኋላ ትዳር አልመሰረቱም ። እንዲያውም የመኖሪያ ቤታቸውን ለባለቤታቸው ማስታዎሻ ይሆን ዘንድ በስማቸው የሚጠራ የመዋዕለ-ሕፃናት ተቋም እንዲሆን ለአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ከአስረከቡ በኋላ ፥ እስከ ዕለት ሞታቸው ድረስ ቃልኪ-ዳናቸውን አክብረውና ጠብቀው ኖረዋል። .

ክቡር ሀዲስ ዓለማየሁ ፥ለእኔም፥ በመርኅ ላይ የተመሠረተ ህይወትና ባኅሪ እንዲኖረኝ የሚያስችለኝን ምክር ሰጥተውኛል ። እንዲህም በማለት መክረውኛል ። እጠቅሳለሁ።

> " ተገኘ፥ በነባቢትም ሆነ በድርጊት የምትፈፅማቸውን ሁሉ፥ ሰው ይወደኛል ወይም የጠላኛል ብለህ አታድርግ ። ሰው ይወደኛል ብለህ የምታደርግ ከሆነ፥ምናልባት ለጥቅምና ለመወደድ ብለህ ሊሆን ይችላል።ይህን ካደረግህ እበላ ባይነትን ልታነፀባርቅ ትችላለህ ። በአንፃሩ ደግሞ ሰውን በመጥላት ስትልም አንዳች ተግባር አትፈጽም። በጥላቻ ላይ የተመሰረተ አድራጎት ምናልባት ሳታውቀው ወደ በቀል ርምጃ ያመራህ ይሆናል ። ምንም ጊዜም መፈጸም ያለብህ ከኅሌናህ ወቀሳ ነፃ የሚያደርግህን ብቻ መሆን አለበት። ሁል ጊዜ ለኅሌናህ ብቻ ተገዥ ሁን። " ሲሉ መክረውኛል።

በሃያኛው ምዐተ-ዓመት ውስጥ በነበረችው ኢትዮጵያ ሀገራችን አንፀባራቂ የታሪክ ምዕራፍ አስመዝግበው ያለፉትን የክቡር ሀዲስ አለማየሁን መቶኛ ዓመት የልደት ቀን ለማክበር በተዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ ይችን አጭር ምስክርነት ለመስጠት ዕድሉን ስላገኘሁ ፥ የሲፖዚየሙን አዘገጆች በድጋሜ አመሰገናለሁ ። ኢትዮጵያ ሀገራችንም በዚህ በያዝነው ሃያ አንደኛው ክፍል ዘመን አያሌ ሀዲስ ዓለማየሆችን እንድታፈራ እምኝላታለሁ ።

አመሰግናሉ!

ተገኘ ሞገስ
ጥቅምት 2002 ዓም
ዋሽንግቶን ዲሲ